# የለውጥ ወኪሎች እና የሰላማዊ እርምጃ

## Agents of Change and Nonviolent Action

**Hardy Merriman**

Conservation Biology, Volume 22, No. 2, April 2008
Translation: Translated by Yohanes Molla and reviewed by Abebe Gellaw

# የለውጥ ወኪሎች እና የሰላማዊ እርምጃ

**በሃርዲ ሜሪማን**[1]
**ትርጉም ዮሃንስ ሞላ / አርታኢ አበበ ገላው**

የሰላማዊ ትግል እርምጃ ተራ ሰዎች ለመብቶቻቸው፣ ለነጻነት እና ለፍትህ የሚፋለሙበት መንገድ ነው። ብዙ ጊዜ ከምግባራዊና ግብረገባዊ ሰላማዊ ትግል ጋር ተያይዞ የሚታይ ቢሆንም፥ እዚህ ጽሁፍ ላይ፣ በግጭት ወቅት ተጽህኖ ለመፍጠር እንደሚያስችል ተጨባች መንገድ እንዴት እንደሚሰራ ለማስፋት፥ ከሌሎች ምግባራዊና ግብረገባዊ መሰረቶች ተለይቶ፣ ራሱን እንደቻለ ክስተት ተመልክቼ ለማየት እሞክራለሁ።

የሰላማዊ ትግል እርምጃ መሰረት፥ በአንድ ማህበረሰብ ስልጣን የሚመነጨው ከሰዎች ፈቃድ እና መታዘዝ ነው ከሚለው እይታ ነው። በንጽጽር፥ ነባራዊው አመለካከት፥ ሕብረተሰብ ውስጥ ያለው ስልጣን የተከማቸ ሀብት እና ሃይልን የመጠቀም አቅም ያለው ማንም ሰው ነው የሚለውን እሳቤ መሰረት ያደረገ ነው። ነገር ግን፥ ልክ ምጣኔ ሀብት፣ የምድረ ሕይወት ንውስ ስርዓት ተገዥ እንደመሆኑ ሁሉ፥ በገንዘብ እና ሃይልን በመጠቀም አቅም ላይ የተመሰረቱ የሚመስሉት የስልጣን ስርዓቶችም፥ በሺህዎች ወይም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች ሰፊ የሆነ የባህርይ እና የመታዘዝ ዝንባሌ ስርዓቶች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ታማኝነታቸውን፣ ጠባያቸውን እና የመታዘዝ አቅጣጫውን ከለወጡ፣ ሕብረተሰብ ውስጥ እንዲሁም በዓለም ላይ ያለው የስልጣን ሚዛንም እንዲሁ አቅጣጫውን ይለውጣል። በቀላሉ ስናስቀምጠው፥ ሰዎች እስካልታዘዙ ድረስ፣ መሪዎች እና ድርጅቶች መምራት አይችሉም ማለት ነው።

ስለዚህ ሰላማዊ እርምጃዎች፥ የሰዎችን የታማኝነት፣ በህብረት የባህርይ እና የታዛዥነት ሁኔታ የሚለወጥበትን መንገድ የመፍጠር፥ አቅማቸውን ይጠቀማሉ። ይኽ በጣም በፍጥነት ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ፥ የህንድ የነጻነት ትግል፣ የአሜሪካ የዜግነት መብቶች እንቅስቃሴ (US Civil Rights Movement)፣ ሌሎችም በርካታ የሰራተኛ ትግሎች—በ1960 አጋማሽ የነበረው፥ የተባበሩት የእርሻ ሰራተኞች እንቅስቃሴ (United Farm Workers) እንዲሁም የ1986ቱ የፈርዲናንድ ማርኮስ ውድቀት፣ አጉስቶ ፒኖቼ፣ ከ1980ዎቹ እስከ 1990ዎቹ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የነበረው አፓርታይድ፣ በ2000 ስሎቦዳን ሚሎሰቪክ፣ እና በ2004 የዩክሬን አምባገነናዊ ስርዓትን...መጥቀስ እንችላለን። ወይንም ደግሞ፥ ሰዎች በአቅራቢያቸው ካሉ የንግድ ተቋማት መካከል የት ሄደው እንደሚገበዩ ሲመርጡ፣ አንድን ምርት ላለመግዛት ሲወስኑ፣ ወይም አማራጭ ተቋማትና እና የምጣኔ ሀብት ምንጮች ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ሁሉ፥ ለውጦቹ በጣም ዝግ ባለ መልኩ ሊከሰቱ ይችላሉ። ምንም እንኳን ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንገዶች እና መገለጫዎች ቢኖሩትም፣ ሁሉም የሰላማዊ ትግል እርምጃዎች ከእነዚህ ከሶስቱ በአንዱ ውስጥ ይመደባሉ። አንደኛው፥ የማይፈቀዱ ድርጊቶችን መፈጸም (acts of commission): ሰዎች ያልተጠበቀባቸውን፣ ወይም ያደርጋሉ ተብሎ የማይታሰብ እና ያልተፈቀደላቸውን ሲያደርጉ ነው። ሁለተኛው፥ ያለመታዘዝ ድርጊት (acts of omission): ሰዎች የሚጠበቅባቸውን፣ ያደርጋሉ ተብሎ የሚታሰበውን ወይም እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን የማያደርጉበት ሁኔታ ነው። ሶስተኛው ደግሞ የሁለቱም ጥምር ድርጊት ነው።

በሰዎች ታዛዥነት እና የባህርይ ሁኔታ ዙሪያ ለውጥን ለማስረጽ፥ ከሁሉም በፊት፣ ሰዎች ሰጥ ለጥ ብለው የሚታዘዙበትን እና ባህርያቸው በዚህ መልኩ የሚቀረጽበትን ምክንያት መረዳት ያስፈልጋል። ምክንያቶቹ ከሕብረተሰብ ሕብረተሰብ ይለያያሉ፤ ነገር ግን፥ በዓለም ዙሪያ ከለውጥ አራማጆች እና አደራጆች በነበረኝ የስራ ግንኙነቶች እንደተረዳሁት፥ የኃሉት ዋነኛ ሁለት

[1] ይህ ጹሁፍ ትንሽ ቀየር ባለመልኩ በ Conservatiom Biology ቅጽ 22 ቁ. 2 ታትሞ የነበረ ነው።

ምክንታዮች ሰዎች ከነባራዊው ባህርይ የተለየ አማራጭ ባህርይ የለም ብለው ማሰባቸው እና፣ የእነሱ ተግባር ወይም ድርጊት ልዩነት ይፈጥራል የሚል በራስ መተማመን ማጣታቸው ነው። ብዙ ሰዎች፥ ሕብረተሰባቸው ውስጥ እውነተኛ አቅም (power) ያላቸው መሆናቸውን ይዘነጉታል። በርግጥ፥ መደበኛ ትምህርት፣ ኮርፕሬሽኖች፣ መንግስታት እና የመገናኛ ብዙሀን በጋራ፥ ስልጣን ወይም ኃይል የመንግስት ስርዓት ውስጥ ባሉ የተወሰኑ ግለሰቦች ወይም የኮርፕሬሽን ዋና ጽ/ቤቶች ውስጥ ነው የሚለውን እና በበላይነት የተቆጣጠሯቸው ገንዘብ እና ጠብመንጃ፣ የመጨረሻው የጥንካሬ ምንጮች እንደሆኑ የሚያትቱትን ትርክቶች ያጠናክራሉ። እነዚህ ትርክቶች ለአላማቸው በደንብ ተስማሚ ናቸው። በታሪክ ውስጥ የሚታወሱት ስኬታማ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴዎች፥ ሰዎች በጋራ በሚያደርጓቸው ተግባራት አማካኝነት፣ በጋራ ራዕይ ዙሪያ የተሰባሰቡ እና በብልሀት የሚተገብሩ ሕዝቦች ከጠላቶቻቸው እና ከገንዘብ በላይ እጅግ በጣም ጠንካራ የመሆናቸውን እውነታ በተመለከተ ንቃተ ኅሊና ፈጥረዋል። ቀልብ መሳብ የሚፈልጉ የዘመኑ ህዝባዊ ንቅናቄዎች ይኽንን እውነታ ከግምት መክተት እና ሰዎችንም በጣም አቅም ያላቸው መሆናቸውን ሊያስታውሱ ይገባል።

ይኽንን አንድ ደረጃ ከፍ አድርገን ስንመለከተው፥ ስኬታማ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ሰዎች አቅምና ኃይል እንዳላቸው ከመንገር ባሻገር፣ ግልጽ እና ሊሳኩ የሚችሉ ዓላማዎችን በማስቀመጥ፣ እንዲሁም ያገኟቸውን የድል ታሪኮች በአግባቡ በመመዝገብ እና ይፋ በማድረግ፥ የሰዎችን አቅም እና ኃይል ግልጽ አድርገው ያሳያሉ። ምናልባት የተገኙት ድሎች ውስን ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን፥ ሰዎችን ለማንቀሳቀስ እና ለክተት ለማሰማራት ያላቸው ተጽህኖ ግን በጣም ከፍተ ነው። ለምሳሌ፥ የአሜሪካ የዜግነት መብት እንቅስቃሴ አቅሙን በሞንጎመሪ እና አላባማ ውስጥ፣ ከ1955 እስከ 1956 ድረስ የአውቶብስ አገልግሎቶችን በዘር ክፍፍል ላይ የተመሰረት እንዳይሆን ለማድረግ፣ እንዲሁም በ1960 ናሽቪል ውስጥ በተመሳሳይ የምሳ ላይ የዘር ክፍፍልን ለማስቆም የተደረጉ እንቅስቃሴዎችን መሰረት በማድረግ ነበር ጥንካሬውን ያካበተው። የህንዳውያን የነጻነት እንቅስቃሴ፣ ከ1930 እስከ 1931 የጨው ህግ (Salt Act) የሚባለውን (ከእንግሊዝ ዜግነት ውጭ ላላቸው ሰዎች ጨው የማምረትም ሆነ የመሰብሰብን መብት የሚያግድ ህግ) እና ሌሎች ህጎች ላይም እግዱን ማስቀልበስ ላይ ነበር ያተኮረው። እነዚህ ዓላማዎች፥ በአጠቃላይ በደቡብ የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ ከነበረው መጠነ ሰፊ የሆነ የዘር መከፋፈልን ለማስቀረት ከተደረጉት እንቅስቃሴዎች ወይም ህንድ ውስጥ ነጻነትን ለመቀዳጀት ከተደረጉት ጋር ሲነጻጸሩ ትንሽ ነበሩ። ነገር ግን፥ የእነሱ እውነተኛ ተጽህኖ እንቅስቃሴዎቹን በማቀጣጠል የነበራቸው ጉልህ ሚና ነበር። እነዚህ ድሎች፥ የሕዝቦች የተግባር እንክስቃሴ ዋጋ እንዳለው እና ልዩነቱን የመፍጠር አቅም እንዳላቸው አሳይተዋል። ይኽም፥ ድጋፍ እና ክተትን በማስተባበር ረገድ ከፍተኛ የሆነ እድገት እንዲያሳይ፣ እና እንቅስቃሴዎቹን ወደ ብሔራዊ እና ዓለማቀፋዊ ማዕከላዊ መድረኮች ገፍቷቸዋል።

እነዚህ ዓላማዎች የተሳኩት የአሜሪካ የሕዝባዊ መብቶች እንቅስቃሴ ወይም የህንድ የነጻነት እንቅስቃሴ ከፍተኛ የሆነ የሞራል ልእልና በመያዙ አልነበረም። ነገር ግን፥ በጠንካራ ስራ፣ በፈጠራ እና ክህሎት በተሞላበት የፖለቲካ ትንታኔ ምክንያት ነው ዓላማዎቹ የተሳኩት። ይኽ የሌሎች ስኬታማ ሰላማዊ እንቅስቃሴዎችም እውነታ ነው። ሆኖም ግን፥ ብዙ ሰዎች ይህንን እውነታ ችላ በማለት፣ የሰላማዊ ትግል ተግባራት የሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ቁጣን መግለጽ እና የኅሊና ዕግዶችን ያካተተ ስለሆነ ነው የተሳካው ብለው ያስባሉ፤ አልያም ስኬታቸው የተወሰነው ልዩ ለዛ ባላቸው መሪዎች ወይም በሆነ ዓይነት ምትሀታዊ ኃይል የተነሳ ነው ብለው ያስባሉ። ሆኖም ግን አይደለም። ቁርጠኛ የሆኑ የማረጋጋት ወይም የስነምግባር ሰላማዊ ትግል አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎችንም አይፈልግም። ነገር ግን፥ የሰላማዊ ትግል ስኬት የሚፈልገው፣ ሁሉንም ያሳተፈ እና ሕዝቦችን አንድ የሚያደርግ ራዕይ፣ ስሜት የሚሰጥ ስልታዊ ዕቅድ፣ ውጤታማ የሆነ የሕዝብ ግንኙነት፣ እና ለሁኔታው የሚስማሙ ትክክለኛ የሆኑ መንገዶችን መለየት ነው። ሆኖም፥ ለሁሉም ቦታ እና ሁኔታ ልክክ የሚል አንድ ወጥ ሁኔታ ወይም መመሪያ የለም። ሰላማዊ የትግል ተግባራት እንደቦታው የሚወሰኑ ናቸው። እንደ፥ አቅም በመስማማት እና በታዛዥነት ይወሰናል እንደሚለው ዓይነት፣ ይህንን እውን የሚያደርጉት አስተሳሰቦች፣ ተግባራዊነቱ በማኅበረሰቡ ዐውድ እና ዝርዝር ሁኔታ የሚወሰን ነው። ድፍረት የተሞላበት ሕዝባዊ ተግባርም ሆነ፣ ንድፍ እና ሁኔታዎችን የሚወስኑ ረቂቅ ለውጦችን፣ ወይም ሁለቱንም የሚያሳይ

ቢሆን፣ ሕዝቦች ስር በሰደደ ተቃውሞ በተለያየ ደረጃ እንዲሳተፉ የሚያስችላቸው፥ የፖለቲካ ምህዳርን ማህበረሰባቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ወይም እንዲፈጥሩ መንገድ ይሰጣል።

እንደ እድል ሆኖ፥ ሰዎች ትልልቅ ውጤቶችን ለማግኘት የሰላማዊ ትግል ተግባራትን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸውና፣ በታሪክም እንዴት ተጠቅመውት እንደነበር የሚያሳዩ፥ ብዙ ምሁራዊ ስራዎች፣ ምርምሮች እና ግንኙነቶች ተከናውነዋል። የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ያለውን ኃይልና አቅም በተገነዘቡት ሰዎች ዘንድም፣ የእንደዚህ ዓይነቱ እውቀት ፈላጊነት ጨምሯል። ምናልባት በዚህ ዙሪያ ብዙ ጋዜጦች ጽፈው አታነቡ ይሆናል፣ ወይ ደግሞ በዚህ ዙሪያ የሚናገሩ ብዙ ፖለቲከኞች ላይኖሩ ይችላሉ፤ ነገር ግን፥ መተራው ህዝብ መሃል ያሉ አደራጆችን እና በዓለም ዙሪያ ያሉ የሕዝባዊ ማኅበር አባላትን ብትጠይቋቸው ይነግሯችኋል። እነዚህ ሰዎች፥ የለውጥ አቀላጣፊ ወኪሎች ሕብረተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች መሆናቸውንና፣ ያ መዋቅራዊ ለውጥም መሰረቱ ላይ በመገንባት የተፈጠሩ መሆናቸውን ተገንዝበዋል። ማንም መጥቶ እንዲመራቸው አይጠብቁም። ምክንያቱም፥ አብዛኛው መንግስት ወይም የኮርፖሬት መሪዎች፥ የአመራር ቦታቸውን፣ ሕዝብ ከተሳትፎ ሲቆጠብ፥ ትክክል የሆነውን ነገር ለማድረግ ቀድመው እንደማይገኙ ተረድተዋል። እንዲሁም እነሱን ተጠያቂ ለማድረግ የሚችሉበትን መንገድ አያውቁም።

ስለዚህ፥ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሕዝቦች፣ ማኅበረሰባቸው የሰብዓዊ መብቶችን፣ ነጻነትን፣ ፍትህን፣ ግልጽነትን፣ የሴቶችን መብቶች፣ የአናሳዎችን መብቶችን እና የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ አቅምና ኃይልን እንዲቀዳጁ፣ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ዘዴ፥ ከፍተኛ በሆነ መልኩ ዐይኖቻቸውን ወደ ሰላማዊ ትግል ተግባራት አዙረዋል። እነዚህን የሰላማዊ ትግል ተግባራት፥ ምናልባት ከድምጽ መስጠት ጋር፣ ከህግ ስርዓት ጋር ወይም ከሌላ ልማዳዊ የለውጥ ማቀላጠፊያ መንገዶች ጋር በማቀናጀት ሊጠቀሙት ይችላሉ።

የሰላማዊ ትግል ተግባር ጥቅም ላይ የሚውልበት ዓላማ ምን ሆነ ምን፥ ቅድመ ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። ይኸም፥ የኃይልን ወይም የአቅምን ግንዛቤ በሰዎች አእምሮ ውስጥ በድጋሚ ማስረጽ ነው። ይኸንን እውቀት ማጋራት እና ሕብረተሰቡን ለራሱ አቅም እና ኃይል ማንቃት፥ የሰብዓዊነትን መንገድ አቅጣጫ ለማስቀየር በጣም ጠቃሚ ግብር ነው።